# የኢትዮ እድር

# የመተዳደሪያ ደንብ

360 Grand Ave., No. 304, Oakland, CA 94610
Tel. 510.663.2100
ethioeder1986@gmail.com

# የኢትዮ እድር የመተዳደሪያ ደንብ

ኢትዮ አድር እንደ አውራፕያውያን አቆጣጠር በ1988ዓም በኦክላንድ ከተማ ተቋቋመ ይህም ማኅበር ከዘር፣ ከጎሣ፣ ከብሔር፣ ከሃይማኖት ፣ከጾታ እንዲሁም ከፖለቲካ ልዩነት ነፃ የሆነ እና በእኩልነት ላይ በታላቁ የቤይ ኤሪያ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮ አሜሪካን የአባልነት ግዴታቸውን ለሚያሟሉ ቤተሰቦች እና ግለሰቦች የተቋቋመ ድርጅት ነው። ይህ ከዚህ በታች ከአንቀጽ አንድ እስከ አስራ አምሥት ድረስ የኢትዮ እድር ተብሎ ለተሰየመው ማኅበር የወጣ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ነው።

ይህም ደንብ ለመንግሥት በተመዘገበው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ያሉትን ሕግጋት ተመርኩዞ ለውስጥ መተዳደሪያ ደንብ እንዲውል ተብሎ በጠቅላላው ማኅበርተኛ ትወያይቶና ተስማምቶበት የተወሰነ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ነው።
ይህም ደንብ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው በአባላቱ ሊለወጥና ሊሻሻል ይችላል። ይህንን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል ወይንም ለመለውጥ አባላቱ በድምጽ ብልጫ (simple majority) አሳልፎ በሚወስነው ውሳኔ መሠረት ይሆናል።

## አንቀጽ አንድ

<u>የእድርተኛ ትርጉም</u>

እድርተኛ ወይም የእድሩ አባል ማለት በመጀመሪያ የኢትዮ እድርን የመተዳደሪያ ደንቦች እና ሕግጋትን የሚያከብር ቀጥሎም ሙሉ ማኅበርተኛ ለመሆን መደበኛውን የመግቢያ ክፍያውን ያጠናቀቀ (አምስት መቶ ዶላር) እና የአባልነት ወርሃዊ ክፍያውን (ሃያ አምስት ዶላር) በየወሩ ባለማቋረጥ የከፈለ ማለት ነው።

በእድርተኛ ሥም የሚጠቃለሉ የቤተሰብ አባላት ባል ሚስት እና ከ21 አንድ ዓመት በታች ሆነው ከማኅበርተኛው አባል ጋር በአንድ አድራሻ የሚኖሩ/የማይኖሩ ልጆች ናቸው።

1. ባል እና ሚስት ማለት በሕግ ተጋብተው ሳይፋቱ ወይም ሳይለያዩ በአንድ ቤት ወይም በአንድ አድራሻ አብረው የሚኖሩ ባለ ትዳሮች ማለት ነው።
2. በተጨማሪም አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ሳይጋቡ በአንድ ቤተሰብ ወይም በአንድ አድራሻ ከሁለት ዓመት በላይ በካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ አብረው የሚኖሩ ማለት ነው።
3. ማኅበሩ እንደአስፋላጊነቱ አመልካችን ወይንም አንድ ማኅበርተኛን ባልና ሚስት መሆናቸውን እና መጋባታቸውን ለማረጋገጥ ከፈለገ ማስረጃ ወይም የጋብቻ ምስክር ወረቀት ለመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው።
4. ልጆች ማለት እድሜያቸው ከ21 አንድ ዓመት በታች ሆነው ከማኅበርተኛው አባል ጋር በአንድ አድራሻ የሚኖሩ/የማይኖሩ ማለት ነው።
5. እድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች የሆኑ የጉዲፈቻ (Adopted) ልጆች እንደ ዋናው የአባል ልጆች ይቆጠራሉ።
6. እድሜያቸው ከሃያ አንድ ዓመት በላይ ሆኖ ከዋናው አባል ጋር አብረው የሚኖሩ/የማይኖሩ የአባል ልጆች ግን እንደ ቅርብ ዘመዶች ይቆጠራሉ።

ባልና ሚስት ማለት በማኅበሩ ሕግ መሠረት አባል ሆነው አብረው ማኅበሩ ውስጥ ገብተው ከተገለገሉ በኋላ በሕግ ተፋተው ወይም
ተለያይተው (divordced or separted) መኖር ከመረጡ እንደ አንድ ቤተሰብ አባል መቆጠራቸው ይቀር እና አባልነታቸውን መቀጠል ከፈለጉ የመመዝገቢያውን ክፍያ ሳይከፍሉ መደበኛውን የወር ክፍያ ብቻ በየግላቸው እየከፈሉ አባልነታቸውን ማስከበር ይችላሉ።

# አንቀጽ ሁለት

<u>የቅርብ ዘመድ ትርጉም</u>

የቅርብ ዘመድ ማለት የዋንኛው አባል ባል/ሚስት፣አባት፣ እናት፣ ወንድም እና እህት ማለት ነው።

1. ከዚህ በላይ የተጠቅሱት የቅርብ ዘመዶች ካለምንም የገቢ ምንጭ በጥግኝነት በዋናው አባል ቤት ውስጥ የሚኖሩ መሆን አለባቸው።

2. በአንቀጽ አንድ ከተጠቀሱት የአባል ልጆች ሌላ እድሜያቸው ከሃያ አንድ ዓመት በላይ ሆኖ ከዋናው አባል ጋር የማይኖሩ የአባል ልጆች (Adopted) በሙሉ ጥገኝነት እንዳሉት የቅርብ ዘመዶች ይቆጠራሉ።

# አንቀጽ ሦስት

<u>የሞት አደጋ ትርጉም</u>

በአንቀጽ አንድ ወይም ሁለት የተዘረዘሩት አባላት ወይም ጥገኞች ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ ማኅበሩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ይሰጣል።

የሥራ አመራር ኮሚቴ ከሟች የቤተሰብ ተወካይ ጋር ተመካክሮ ለኢትዮ እድር አባላት የሐ ዘኑን ሥነ ሥርዓት በሚመለከት በታላቁ የቤይ ኤሪያ ለሚኖሩ የእድሩ አባላት አስፈላጊውን መልእክት ያስተላልፋል።

የእድሩ ኮሚቴ ስለ ቀብሩ አፈጻጸም የሚደረግ ዝግጅት

1. ከቤተሰቡ ወይም ከቤተሰብ ተወካይ ጋር በመተባበር የቀብር ቅድመ ዝግጅቱን ያቅዳል።
2. የቀብር ቦታውን ከሎን ትሪ ጋር በመነጋገር ዝግጁ ማድረግ የእድሩ ተቅዳሚ ተግባር ነው። በተጨማሪ እድሩ ፊዩነራል ሆም አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን በማፈላለግ የሐዘንተኛውን ቤተሰብ በቅርብ በመሆን ይረዳል።
3. አስከሬኑ ወደ አገር ቤት የሚላክ ከሆነ እድሩ የቆንሱላር፣ የአየር መኝኘዣ እና ፊዩነራል ሆም አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችን በማፈላለግ የሐዘንተኛውን ቤተሰብ በቅርብ በመሆን ይረዳል።
4. እድሩ በቤተሰቡ አነሳሽነት ለሚቀርቡ ተጨማሪ የእርዳታ ጥያቄዎች ከቤተሰቡ ተወካይ ጋር በመተባበር ከበጎ አድራጊ ግለሰቦች የገንዘብ መዋጮ አሰባሰብን በሚመለከት ከሐዘንተኛው ቤተሰብ ጋር በቅርብ በመሆን ይረዳል።

# አንቀጽ አራት

<u>በቀብር ወይም በሐዘን ጊዜ የሚሰጥ ድጋፍ</u>

በዋናው እድርተኛ አባል ማለትም ባል ሚስት እና እድሜአቸው ከ21 በታች ሆነው ከማኅበርተኛው አባል ጋር በአንድ አድራሻ ለሚኖሩ/ለማይኖሩ ልጆች/የጉዲፈቻ (Adopted) ልጆች ላይ የሞት አደጋ በሚደርስባቸው ወቅት ከዚህ በታች የተዘረዘረው ድጋፍ ይሰጣል።

የቀብር ቦታ/ Cemetery

1. ማኅበሩ በደንቡ መሠረት ተገቢውን የመቃብር ቦታ ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ ለሟች ቤተሰብ አዘጋጅቶ ያቀርባል።
2. በአሁኑ ወቅት ማኅበሩ ያዘጋጀው የቀብር ሥነ ሥርዓት ቦታ ከዚህ በታች የተጠቅሱትን ቁሳቁስ እና ተግባራትን ብቻ የሚያጠቃልል ይሆናል።
    1. የመቀበሪያ መሬት (Property)
    2. የቀብሩን ቦታ ማስተዳደሪያ (Endowment Care)
    3. የአስከሬን ሳጥን የሚያርፍበት የሲሚንቶ ሳጥን (Grave Box – Vault)
    4. የቀብሩን ቦታ ማዘጋጃ (Intermment Fee)
    5. የቅዳሜ ቀን የሥራተኛ ተጨማሪ ክፍያ (lone tree overtime)
    6. የካሊፎርኒያ የሙት ታክስ (Tax)

- ዋናው አባል እድርተኛ ወይም የሟች ቤተሰብ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ቁሳቁሶች እና ተግባራት ሌላ የማሻሻል እና የመጨመር መብት ቢኖራቸውም ማንኛውም ተጨማሪ ወጪ ግን የሟች ቤተሰብ ኀላፊነት ይሆናል።
- በአሁኑ ጊዜ ማኅበሩ ምንም ዓይነት ተጨማሪ የወጪ እርዳታ አያደርግም።
- የማኅበሩ ባለድርብ (Double Deck) የቀብር ጉድጓድ ሁለት ሰው ከላይ እና ከታች እንዲስቀብር ሆኖ ስለተዘጋጀ እንደ ማኅበሩ ቤተሰቡ አባል ቅደም ተከተል ሆኖ ይቀበራል ማለት ነው።
- አንድ ቤተሰብ የማኅበሩ ባለድርብ (Double Deck)የመቃብር ጉድጓድ ቮልት በሁለት ሟች ቤተሰቦች በሙሉ ጥቅም ላይ ሳይውል ሳይሞላ አዲስ ባለድርብ የመቃብር ጉድጓድ ቮልት ማስከፈት ወይም መያዝ አይችለም።
- ማንኛውም የማኅበር ዓባል የመቀበሪያውን መሬት የመሸጥ፣ የመለወጥ እና ወደ ሌላ ሰው የማስተላለፍ ሙብት የለውም።

አሰከሬን አዘጋጅ እና አቅራቢ (Funeral Home)

- ማኅበሩ አስከሬን ለቀብር ከሚያዘጋጁ ድርጅቶች ከፊዩነራል ሆም ጋር የሟች ቤተሰብን አገናኝቶ ከማስተባበር በስተቀር በጠቅላላው ጉባኤው ከተወሰነው $1,000.00 ዶላር ሌላ ተጨማሪ ክፍያ ከማኅበሩ ለጊዜው ወጪ ሆኖ አይሰጥም።
- በተጨማሪም ለእንግዳ ማስተናገጃ እንዲሆን $500.00 ዶላር ለሟች ቤተሰብ ወጪ አድርጎ ይሰጣል።

4.2.1.1 ማኅበሩ ባዘጋጀው የቀብር ቦታ መቀበር ለማይፈልግ በጥሬ ገንዘብ $4,000.00 ዶላር ለሟች ቤተሰብ እንደ አስፈላጊነቱ እንዲያውለው ከማኅበሩ ወጪ ሆኖ ይሰጣል።

4.3 የእድርተኛው የቅርብ ዘመዶች እና እድሜያቸው ከ21 ዓመት በላይ ያላቸው የአባል ልጆች ከአባል ጋር በአንድ አድራሻ አብረው የሚኖሩ/ የማይኖሩ የአባል ጥገኞች በአንቀጽ ሁለት በንኡጽ አንቀጽ ሁለት ነጥብ አንድ የተዘረዘሩት በተጨማሪም በአንቀጽ ሁለት ነጥብ ሁለት የተጠቀሱት የአባል ልጆች የሞት አደጋ ቢያጋጥማቸው ለሐዘን መስተንግዶ አምስት መቶ ዶላር ከማኅበሩ ወጪ ሆኖ ይሰጣል።

4.5 <u>ከአንድ ዓመት በታች በአባልነት የቆዩ አባላት</u>

እንደ አጋጣሚ ሆኖ በአንድ አዲስ ዓባል ላይ በአባልነት አንድ ዓመት ከመሙላቱ እና የሙሉ አባልነት መብቱ ከመከበሩ በፊት በድንገተኛ አደጋ ወይም በሕመም ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ በአንቀጽ አራት ነጥብ አንድ በተደነገገው መሠረት ለመስተንግዶ ተብሎ የተመደበው $500.00 ዶላር ብቻ ወጪ ሆኖ ለመስተንግዶ ይሰጣል።

በዚሁ አዲስ አባል ላይ የቅርብ ዘመድ ተብሎ በንኡጽ አንቀጽ ሁለት እንደተጠቀሰው በዘመዶቹ ላይ በድንገተኛ የሞት አደጋ ቢደርስ በአንቅጽ ሦስት በንኡስ አንቀጽ ሦስት ነጥብ ሦስት እንደተዘረዘረው ማንኛውም ትብብር ይደረጋል።
ይህ ከዚህ በላይ የተወሰነው የእርዳታ መጠን እንደ ድርጅቱ ገቢ እና ወጪ መጠን በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል።

## አንቀጽ አምሥት

<u>የመርዶ ትርጉም</u>

- መርዶ ማለት የዋናው አባል ባል ሚስት ልጆች፣ አባት፣ እናት፣ ወንድም እና እህት ብቻ ያጠቃልላል።
- ለመርዶ በአንቀጽ አምስት መሠረት ለሟች ቤተሰብ $300.00 (ሦስት መቶ) ዶላር ከማኅበሩ ወጪ ሆኖ ይሰጣል።
- ማኅበሩ እንደ ዋናው አባል ፈቃድ ለእድሩ አባላት በሙሉ መልእክት በማሰራጨት እና ከቤተሰቡ ወይም ከቤተሰቡ ተወካይ ጋር በመሆን
  አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል።

## አንቀጽ ስድስት

<u>የክፍያ አሰጣጥ</u>

1. ዋናው አባል በሞት አደጋ በሚለይበት ሰዓት ለቀብር የተመደበው ወጪ ዋናው አባል በሰጠን መመሪያ መሠረት ገንዘቡን ለቤተሰቡ ተጠሪ ወይም ተወካይ ይሰጣል።
2. በአጋጣሚ ከእዚህ ዓለም በሞት የተለየው የሁለቱ ወይም የሦስት ማኅበርታኞቻችን ዘመድ ከሆኑ የእርዳታ ክፍያው የሚሠጠው አስከሬኑ ለወጣበት ወይም ሐዘን ለተቀመጡበት አባል ቤት ብቻ ነው።
3. በአንድ ሐዘን ሁለት ወይም ሦስት ወጪ ሆኖ ከማኅበሩ ምንም ዓይነት እርዳታ አይሰጥም።
4. ዋናው ማኅበርተኛ የሚደርሰውን የገንዘብ እርዳታ አልፈልግም ካለ ገንዘቡ ለማኅበሩ ተመልሶ ከምሥጋና ጋር ገቢ ይሆናል።
5. ማንኛውም የእድር አባል የደረሰብትን የሐዘን ወይም መርዶ ለእድሩ በስልክ ወይም በጽሑፍ በአርባ አምሥት ቀን ውስጥ ካላስታወቀ ከአርባ አምሥተኛው ቀን ካለፈ በኋላ ምንም ዓይነት ክፍያ አይደረግም።

## አንቀጽ ሰባት

<u>የኢትዮ እድር አባልነት መስፈርቶች</u>

አንድ የቤይ ኤሪያ ነዋሪ የሆነ ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮ አሜሪካን ማኅበርተኛ ለመሆን በሚጠይቅበት ሰዓት ማኅበርተኛ ለመሆን ከዚህ በታች የተገለጹትን ሁናቴዎች ማሟላት አለበት።

1. በእድሜው ከ21 ዓመት በላይ የሆነ
2. በቅድሚያ አመልካች ማመልከቻ ቅጽ ማስገባት አለበት።
3. ማመልከቻው በማኅበሩ ቦርድ ተጠንቶ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ የሚከተለውን ግዴታዎች ማሟላት አለበት።
4. የኢትዮ እድር እና የአዲስ አባል የስምምነት ሰነድ፣

5. የአዲስ አባልነት የመመዝገቢያ $500.00 ዶላር ክፍያ፣
6. የስድስት ወር የአባልነት ወርሃዊ ክፍያ ($25.00) በቅድሚያ በድምሩ $150.00 ዶላር መከፈል አለበት።
7. ማንኛውም አዲስ ማኅበርተኛ ሙሉ መብቱ እና ሙሉ ተጠቃሚነቱ የሚከበርለት የመመዝገቢያውን እና ዓመታዊ የዓባልነት ጠቅላላ ክፍያውን $800.00 ዶላር በአንድ ዓመት ወስጥ አጣናቅቆ ሲከፍል ብቻ ነው።
8. አንድ አዲስ ማኅበርታኛ በድርጅቱ ተቀባይነትን ካገኘ በኋላ የአባልነት መመዝገቢያና የወር ክፍያውን ከላይ ባለው ሁኔታ ለመክፈል ይከብደኛል ብሎ ካስታወቀ ማኅበሩ ጉዳዩን አጥንቶ አማካኝ የሆነ ከአንድ ዓመት ያልበለጠ የተራዘመ የክፍያ መፍትሔን (installment payment) በመፈለግ ይተባበራል።
9. በዚህ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ይህ አዲስ አባል የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ አንብቦ የመረዳት እና እንዲሁም የመጠየቅ ኃላፊነት አለበት።

# አንቀጽ ስምንት

<u>ስለ አባላት ክፍያ</u>

የአባላት ክፍያ ዓመቱ ለሁለት ተከፍሎ በዓመት ሁለት ጊዜ $150.00 (አንድ መቶ ሃምሣ ዶላር) በጠቅላላው በዓመት $300.00 (ሦስት መቶ ዶላር) ይከፈላል። የመጀመሪያ ክፍያ በወር ሃያ አምሥት ዶላር ለስድስት ወር January 1st – June 30th (ከጃንዋሪ አንድ እስከ ጁን ሰላሳ) መጨረሻ ይሆናል።

የሁለተኛው ክፍያ በወር ሃያ አምሥት ዶላር ለስድስት ወር July 1st – December 31st (ከጁላይ አንድ እስከ ዲሴምበር ሰላሳ አንድ) መጨረሻ ይሆንና የዓመቱ ክፍያ በድምሩ ሦስት መቶ ዶላር ይሆናል።

<u>የክፍያ ግዴታዎች</u>

ከዚህ በታች ያሉትን ግዴታዎች ያላሟላ አባል ምንም ዓይነት የማኅበሩ ድጋፍ ወይም እርዳታ አያገኝም።

1. ከዘጠና ቀናት (ሦስት ወር) በላይ የማኅበር ክፍያውን ሳይከፍል ወደ ኋላ የቀረ አባል የ$25.00 (ሃያ አምሥት) ዶላር መቀጫ ይከፍላል።
    - በዚህም ክፍያውን ባላሟላበት ወቅት አንድ አደጋ በእድርተኛው ወይም በቤተሰቡ ላይ ቢደርስ በሕጉ መሠረት ክፍያ ፣ድጋፍ ወይም እርዳታ አይደረግለትም።
2. ከአንድ መቶ ሃያ ቀናት (ከአራት ወር) በላይ ሳይከፍል ወደኋላ የቀረ ማንኛውም ማኅበርተኛ: ከማኅበሩ በገዛ ፈቃዱ እንደተሰናበተ ተቆጥሮ ማንኛውም ዓይነት ድጋፍ ወይም እርዳታ ከማኅበሩ አያገኝም ከአባልነትም ይወገዳል።
    - ነገር ግን ይህ አባል ማኅብሩ ውስጥ ተመልሼ ገብቼ የማኅበሩን ድጋፍ እና እርዳታ መቀጠል እፈልጋልሁ ቢል የሃምሣ ዶር መቀጫ እና ወደ ኋላ የቀረበትን ውዝፍ ክፍያ ክፍሎ መመለስ ይችላል።
3. አንድ ማኅበርታኛ የአባልነት የወር ክፍያውን ለመክፈል ለጊዜው በሕመም ሆነ በተለያዩ የግል ጉዳዮች ምክንያት አቅም አጥቼአለሁ ብሎ ለቦርዱ በጽሑፍ ካስታወቀ የማኅበሩ ቦርድ የዚህን የማኅበርተኛ ጉዳይ አጥንቶ እና ተወያይቶበት ለጊዜው መክፈል ያለመቻሉን ከተረዳ በኋላ አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል።
    - ነገር ግን ይህ አባል ከጊዜ በኋላ ሙሉ ጤናውን አግኝቶ ወደ ሥራ ዓለም ተመልሶ ገቢ ማግኘት ከጀመረ እንደማንኛውም አባል የወር ክፍያውን መክፈል እንዲቀጥል ይጠየቃል።

ቋሚ ስንክልና - Permanent Disability

- አንድ ነባር አባል የሚጠበቅበትን የአባልነት ግዴታውን ያላጓደለ በጽሁፍ በሐኪም የተረጋገጠ አደጋ ሕመም ወይም በሽታ ካጋጠመው እና በግሉም ሆነ ከመንግሥት ምንም ዓይነት የገንዘብ እና የቁስ ድጎማ የማያገኝ መሆኑን እና በገቢ እጥረት ምክንያት በማኅበሩ የተመደበውን የወር ክፍያውን ለመክፈል አቅም የለኝም ብሎ ለቦርዱ በጽሑፍ ካስታወቀ የማኅበሩ ቦርድ የዚህን የማኅበርተኛ ጉዳይ አጥንቶ እና ተገቢውን ምርመራ ካደረገ በኋላ አስፈላጊውን የእርዳታ ውሳኔ ይሰጣል።
- ሆኖም ይህ አባል ከጊዜ በኋላ ሙሉ ጤናውን አግኝቶ ወደ ሥራ ዓለም ተመልሶ ገቢ ማግኘት ከጀመረ ወይም ከመንግሥት የጥሬ ገንዘብ ድጎማ ማግኘት ከጀመረ እንደማንኛውም አባል የወር ክፍያውን መክፈል እንዲቀጥል ይጠየቃል።

በህመም ላይ ስላለ አባል

- በበሽታ ወይም በአደጋ ምክንያት ታሞ ለተኛ የማኅበሩ አባል ፈቃደኛ ከሆነ ማኅበሩ ለሌሎች አባልት አስታውቆ እንዲጠየቅ ያደርጋል።
- እርዳታም ካስፈለገ እና የማኅበሩ አባል ከጠየቀ ማኅበሩ ከሌሎች አባለት መዋጮ ወይም እርዳታ እንዲያደርጉለት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ትብብር ያደርጋል።

# አንቀጽ ዘጠኝ

ቦርድ እና የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ

የቦርድ አባላት

1. ቦርድ አባል በየሁለት ዓመት በጠቅላላው ማኅበርተኛ ይመረጣል ነገር ግን አንድ የቦርድ አባል በአንጻሩ ደግሞ ሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን (አራት ዓመት) ማገልገል ሲችል የአገልግሎቱንም ዘመን ከጨረሰ በኋላ ፈቃደኛ ከሆነና በተለይም በአስመራጭ ኮሚቴ ተመልምሎ ቀርቦ በጠቅላላው ማኅበርተኛ ከተመረጠ እንደገና ማገልገል ይችላል።
   - እነዚህም የቦርድ አባላት በመልማይ ኮሚቴ ይመለመላሉ። መልማይ ኮሚቴው ከአባላቱ ውስጥ የአባልነት ግዴታቸውን ካሟሉት ውስጥ መልምሎ ለምርጫ ያቀርባል።
   - ከዘጠኝ ያልበለጡ ማኅበርተኞች ለቦርድ አባልነት ይመረጣሉ።
   - ከአራት የማይበልጡ አዳዲስ አባላት በየሁለት ዓመት በምርጫ ተመርጠው ለቦርድ አባልነት እንዲያገለግሉ ይመረጣሉ።
   - ቀሪው አምሥት አባላት አዲስ ገቢዎችን በማለማመድ በማኅበሩ የሥራ አስኪያጅ ጉድለት እንዳይኖር የተቻላቸውን ትብብር ለአዲስ ገቢዎቹ ያደርጋሉ።
   - ከእነዚህ ከተመረጡት የቦርድ አባላት ውስጥ ጠቅላላው ማኅበርተኛ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውን ይመድባል።
   - አንድ የቦርድ ዓባል በአንድ ዓመት ውስጥ አስቀድሞ ሳይናገር ከስብሰባ በተከታታይ ሦስት ጊዜ ከቀረ ከቦርድ ይወገዳል።
   - አንድ የቦርድ አባል ከተወሰነለት ጊዜ በፊት ከሥልጣኑ ከወረደ በቦታው ሌላ ማኅበርተኛ በተቀሩት የቦርድ ዓባልት ደምጽ ብልጫ ተመርጦ የውጭውን አባል ጊዜ በመጨረስ ያገለግላል።
   - አንድ የቦርድ አባል ሕገወጥ ነገር ሲሰራ ቢ ገኝ ከቦርድ አባልነት በድምጽ ብልጫ ይሰናበታል።

- ቦርዱ በዓመት ከሦስት ጊዜ ያላነሰ ስብሰባ ያደርጋል።
- ቦርዱ በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የጠቅላላ አባልት ስብሰባ ይጠራል።
- አስቸኳይ ስብሰባ ካስፈለገ ሊቀመንበሩ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውን ቦርዱን ወይም ጠቅላላ አባልትን ለስብሰባ መጥራት ይችላል።

2. የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አመራረጥ
    - በየሁለት ዓመት ይመረጣል
    - የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከቦርዱ ውስጥ ሆነው በቦርድ አባላት የደምጽ ብልጫ ይሾማሉ።
    - የሥራ አስኪያጅ ማለት ከቦርዱ እና ከአባልቱ የሚሠጠውን መመሪያ በመከተል ማኅበሩን ያስተዳድራል።

የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ

ሀ. የቦርዱ ሊቀ መንበር :-አስተዳዳሪ
ለ. የቦርዱ ዋና ጸሐፊ :-ሴክሬተሪ
ሐ. የቦርድ ገንዘብ ያዥ :-ትሬዠረር
በመሆን ከሌላው አባል የተለየ ጥቅም ወይም የደሞዝ ክፍያ ሳያገኙ ማኅበሩን ያገለግላሉ።

- የማኅበሩ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመናቸውን በሚያጠናቅቁበት ወቅት በይዞታቸው የሚገኘውን የማኅበሩን የሚንቀሳቀሱ ሰነዶችን እና ንብረቶች ለሚተኳቸው የሥራ አስኪያጅ ባልደረቦች የማስረከብ ኃላፊነት አለባቸው።

3. የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሥራ መ ደብ ዝርዝር

<u>ሊቀ መንበር</u>

- ከተመ ረጡት የቦርድ አባልት ውስጥ በአባልቱ ድምጽ ብልጫ ይመርጣል።
- ሊቀ መንበሩ የማኅበሩ የበላይ ጠባቂ በመሆን የቦርዱን የሥራ አመራር የማኅበሩን የሥራ አስተዳደር እና የሥራ ዘርፍ አቅጣጫ ይቆጣጠራል።
- ሊቀ መንበሩ የቦርዱን እና የጠቅላላ አባልቱን ሸንጎ ስብሰባ ይመራል።
- ማንኛውንም የማኅበሩን የገንዘብ ወጪ ቼክ ከገንዘብ ያዢው ጋር አብሮ በመሆን ይፈርማል።
- ሊቀ መንበሩም ከቦርዱም ሆነ ከአባላቶቹ የሚሰጠውን መመሪያ ወይም የውስጥ መተዳደሪያ ደንቡን ምርኩዝ በማድረግ እንደ ሆናቴው ማኅበሩን ያስተዳድራል ሥላጣኑን የመጠቀም መብት አ ለው።

<u>ዋና ጸሐፊ</u>

- ከተመረጡት የቦርድ አባላት ውስጥ በአባላቱ በድምጽ ብልጫ ይመረጣል።
- ዋና ጸሐፊው የማኅበሩን ቃለ ጉባኤ መዝገብ ይይዛል።
- በቦርዱና እና በአባሎቹ መካከል ለሚደረገው ግንኙነት ኃላፊ ነው።
- ማንኛውንም የማኅበሩን የግንኙነት ሰነዶች መዝገብ በማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ይይዛል።
- የአባላትን የሥም ዝርዝር በየጊዜው በመከታተል በመዝገብ ይይዛል የዝርዝሩንም መዝገብ በየጊዜው ለኣባላት ይልካል።
- ሊቀ መንበሩ በማይገኝበት ወቅት ጉባኤዎችን ይመራል።
- ከቦርዱም ሆነ ከአባላቶቹ የሚሰጠውን መመሪያ ወይም መተዳደሪያ ደንቡን ምርኩዝ በማድረግ እንደ ሁናቴው ሥልጣኑን ይጠቀማል።

ገንዘብ ያዥ

- ከተመረጡት የቦርድ አባላት ውስጥ በአባላቱ በድምጽ ብልጫ ይመረጣል።
- የማኅበሩን የገቢ እና የ ወጪ ደረሰኞች ሰነዶች መዝገብ ይይዛል።
- ማንኛውንም የማኅበሩን እዳዎች ይከፍላል።
- የማኅበሩን ተን ቀሳቃሽ ንብረቶች እና ጥሬ ገንዘብ በባንክ ያስቀምጣል።
- በማኅበሩ ሥም የሚከፈሉትን ዕዳዎች በቼክ ከሊቀመንበሩ ጋር አብሮ በመፈረም ይከፍላል።
- የአባልትን ወ ርሃዊ ክፍያ በመቆጣጠር ከአባልት ይሰበስባል።
- የማንኛውንም የማኅበሩን እዳዎች ይከፍላል።
- የማኅበሩን የሂሣብ መዝገብ ይይዛል።
- የሂሣብ መዛግብትን እንደ አስፈላጊነታቸው ለቦርዱ፣ ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው እና ለኦዲተሩ በተጠየቀበት ሰዓት ያቀርባል።
- ዓመታዊ የሂሣብ ዝርዝር ዘገባ አዘጋጅቶ ለአባላቱ ያቀርባል።

ኦዲተር

- የኢትዮ እድር ገንዘብ ያዥ የእድሩን ዓመታዊ የሂሣብ ዘገባ ያለ ኦዲት ምርመራ ለጠቅላላው ጉባኤ ቢቀርብ በቂና የሕግ ግድፈትም የማይስከትል በመሆኑ ለወደፊት በዚሁ መሠረት እንዲሠራና የእደሩ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በአንጻሩ እንዲሻሻል May 11, 2013 ዓም በቤቱ ትወስኖ አልፏል።
- ሆኖም ወደፊት በሂሣብ ሥራ የሰለጠነ እና በሂሣብ ምርመራ ልምድ ያለው በአዓባላት የተመረጠ ወይም በጎ ፈቃደኛ ግለሰብ ከተገኘ የእደሩ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በአንጻሩ ተሻሽሎ የእድሩ ዓመታዊ ጠቅላላ የሒሣብ ሰነድ በኦዲተር ተመርምሮ ለዓባላቱ እንዲቀርብ ይደረጋል።

4. የቦርድ አመራረጥ ሁኔታ

- ግዴታቸውን ያሟሉ አባልት ብቻ ለምርጫ ይቀርባሉ።
- የቦርድ ምርጫ በሚደረግበት ወቅት የአባልነት ግዴታውን ያሟላ ቤተሰብ አንድ የምርጫ ድምጽ ብቻ ነው ያለው።
- ቋሚ የሆነ የብቻው የቦርድ አባላት የምርጫ ቀን በጠቅላላ አባላት ስብሰባ ዕለት በአባላቱ ይወሰናል።
- የቦርድ አባልት ምርጫ ቀን የጠቅላላው አባላት ስብሰባ በሆነ ከስደስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይሆናል።
- ቋሚ የሆነ የምርጫ ካርድ ተዘጋጅቶ ለአባላቱ በምርጫው ቀን በአስመራጭ ኮሚቴው ይሰራጫል።
- በምርጫው ቀን ለመገኘት ያልቻለ አባል አስቅድሞ የምርጫውን ካርድ ኮሚቴውን ጠይቆ ምርጫውን በፖስታ ቤት መላክ ይችላል።
- የተላከው ካርድ ትክክለኛ መብት እንዲኖረው ከምርጫው ቀን በፊት በማኅበሩ ጽሕፈት ቤት መድረስ አለበት።
- ከምርጫው ቀን በኋላ የደረሰ የምርጫ ካርድ ሙሉ የምርጫ መብት ያለው አይሆንም።
- ምርጫው በግልጽ ሳይሆን በሚስጥር ይሆናል።

5. ቦርድ እና የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ

- አንድ የቦርድ አባል ወይም የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል የተጣለበትን አደራ የሥራ ግዴታ አንደተጠበቀው ሳያሟላ ቢቀር ቦርዱ ጉዳዩን ተመልክቶ እና አጥንቶ በሁለት ሦስተኛ የድምጽ ብልጫ ውሳኔ ቦርዱ ያንን አባል ከሥልጣኑ ሊያስወግድ ይችላል።
- ቦርዱ እንደ አስፋላጊነቱ የሥራ መደብ ፤እየፈጠረ ሥራውን የሚመሩ ባለ ሥልጣኖች ለመመደብ ይችላል።

6.የቦርድ አባል አመራረጥ

የቦርድ አባል ለቦርድ አባልነት እጩ ሆኖ ለመቅረብ በአባልነት ቢያንስ አንድ ዓመት ባለማቋረጥ አባል ሆኖ የቆየና የአባልነት ግዴታውን ያሟላ መሆን አለበት።

# አንቅጽ አሥር

<u>ኮሚቴዎች</u>

- የማኅበሩ አባላት እንደ አስፈላጊነቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችን በመፍጠር በየሁለት ዓመት አዳዲስ አባላትን እየመረጠ ሥራዎችን እንዲከናውኑ ያደርጋል።
- እነዚህም ኮሚቴዎች የሚመሩት በተለያዩ የቦርድ አባላት ሰብሳቢነት ወይም መሪነት ይሆናል።

<u>የበዓል ዝግጅት ኮሚቴ</u>

- የዚህ ኮሚቴ ተግባሩ ለማኅበሩ ገቢ የሚያስገኝበትን መንገድ አየፈለገ እና ዝግጅቶችን እያካሄደ ለማኅበሩ ገቢ ይፈጥራል።
- በተጨማሪም የማኅበሩ ዝግጅቶች ማቀነባበር እና ማዘጋጀትም ይሆናል።
- ይህ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሲሆን አገልግሎቱ ጠቅላላውን ለማኅበሩ የሚያገለግሉትንም ጎዳዮች ያጠቃልላል።

<u>የአስመራጭ ኮሚቴ</u>

- አስመራጭ ኮሚቴ በመላው አባላት ተመርጦ የሥራ ተግባሩ በየሁለት ዓመት አባልትን ለቦርድ ምርጫ ያቀርባል።
- ኮሚቴው የራሳቸውን ሰብሳቢ ይመርጣሉ።
- የዚህም ኮሚቴ አባላት ተጠሪነታቸው ለጠቅላላው አባላት ብቻ ሲሆን የሥራ ተግባራቸው ግን በሥልጣን ላይ ካለው ቦርድ ጋር በመመካከር እና አብሮ በመሥራት የምርጫውን ፕሮግራም አብረው ያካሂዳሉ።
- ግዴታችውን ካሟሉት አባላት ውስጥ መልመለው ለቦርድ አባልነት ለምርጫ ያቀርባሉ።
- በምርጫው ወቅት ሁልጊዜ ለምርጫው ከሚያስፈልገው አባልት በላይ መልምለው ማቅረብ አለባቸው።
- በምርጫው ቀን የምርጫውን ፕሮግራም ያካሂዳሉ።
    - ግዴታቸውን ያሟሉትን አባላት ይመዘግባሉ
    - የምርጫውን ካርድ ያሰራጫሉ
    - ምርጫው በሕጉ መሠረት መካሄዱን ይቆጣጠራሉ
    - ምርጫው እንዳለቀ አሸናፊ አባላትን በማስታወቅ የምርጫውን ካርድ ይቆጥራሉ
    - የምርጫውን ውጤት ለአባላት ያስታውቃሉ

# አንቅጽ አሥራ አንድ

ከእድሩ በግል ፈቃዳቸው ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ድርጅቱ ለሚያሰናብታቸው አባላት እና በተጨማሪም የሚደርስባቸውን የአባልነት ክፍያ ባለማጠናቀቅ ከማኅበሩ ለሚሰናበቱት እድርተኞች እስከወጡበት ጊዜ ድረስ የከፈሉት ጠቅላላ ገንዘብ ተመላሽ ሆኖ አይሰጣቸውም።

# አንቅጽ አሥራ ሁለት

<u>የሥራ ማስኪያጃ ወጪ</u>

የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ለጥቃቅን ወጪ የሥራ ማስኬያጃ እስከ $250.00 ዶላር ድረስ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እያወጣ ማኅበሩን ማስተዳደር ይችላል። ካስፈለገም ቦርዱ እስከ ሁለት ሺህ ዶላር ድረስ ለሥራ ማስኬያጃ ጠቅላላ አባልትን ሳይስፈቅድ ወጪ ማውጣት ይችላል። በተጨማሪም ቦርዱ እስከ አምሥት ሺህ ዶላር ድረስ ለኣባልት ዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ ዘግጅት ማውጣት ይችላል።

# አንቀጽ አሥራ ሦስት

<u>የአባላት ጠቅላላ ዓመታዊ ስብሰባ</u>

- የአባላት ዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋል
- የአባላት ዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ በየዓመቱ በኤፕሪል ወይም በሜይ ወር በእለተ ቅዳሜ ይደረጋል
- በዚህ ስብሰባ ላይ እያንዳንዱ አባል በስብሰባው ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት
- አንድ አባል ያለበቂ ምክንያት ቀደም ብሎ ቦርዱን ሳያስታውቅ በዓመታዊ የጠቅላላ አባላት ስብሰባ ላይ ያልተገኘ አባል የሃምሣ ዶላር መቀጫ ይደርስበታል።
- በስብሰባው ላይ ምርጫ በሚደርግበት ወቅት ኣንድ ቤተሰብ ያለው ድምጽ አንድ ብቻ ነው።

# አንቅጽ አሥራ አራት

ይህ የወስጥ መተዳደሪያ ደንብ ከዋናው ሴክሬቴሪ ኦፍ እስቴት ጽሕፈት ቤት ከተመዘገበው መተዳደሪያ ደንብ የማይቃረን ወይንም ልዩ ሕግ ሳይሆን ዋናው የመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ላሉት ደንቦች ድጋፍ እና በባሕላችን መሠረት ለአንዳንድ ጉዳዮች ማብራሪያ እየሰጠን ሥራ ማከናወኛ እንዲሆን ተብሎ የወጣ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ነው።

አሻሚ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ዋናው በሴክሬቴሪ ኦፍ እስቴት ጽሕፈት ቤት የተመዘገበው የመተዳደሪያ ደንብ እንደዋናው ሕግ ተወስዶ እንደ መመሪያ እና ሥራ ማስኬጃያ ይጠቀምበታል።

በመንግሥት የተመዘገበው የመተዳደሪያ ደንብ ከዚህ ከውስጥ የመተዳደሪያ ደንብ በላይ ቅድሚያ ይኖረዋል።

# አንቅጽ አሥራ አምሥት

የማኅበሩ ቦርድ ይህንን የወጣውን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በየጊዜው እየተወያየበት እና ድምጽ እየሰጠበት እንደ አስፈላጊነቱ ከዋናው መተዳደሪያ ደንብ ጋር እያስተያየ የማይቃረንበትን መንገድ እየፈለገ ለውጥ ወይም መሻሻል እንዲደረግበት ለጠቅላላው አባላት እንዲወያዩበት እና ድምጽ እንዲሰጡበት ስብሰባ ላይ ያቀርባል።

ይህ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻልም ሆነ ለመለወጥ አባላቱ በድምጽ ብልጫ ሊሽሩት፣ ሊለውጡት ወይም ሊያሻሽሉት ይችላሉ።